# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# የኢየሱስ መፈተን

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S.

Alastair Paterson

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2020 Bible for Children, Inc.
**ፈቃድ**፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ እንዲህ አለ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት”። መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ በእርግብ አምሳል ወረደበት።



ወዲያውም
መንፈስ ቅዱስ
ኢየሱሰን ወደ
ምድረበዳ
መራው።በዚያም
ብቻውን ነበረ።



ኢየሱስም አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ጾመ። ምንም ነገር
አልበላም ነበር።ስለዚህም
በጣም ተራበ።



ልዩ ልዩ አራዊትም አብረውት
እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ
ያስተምራል።



ዲያብሎስም ኢየሱስን ሊፈትነው
መጣ።ከብዙ አመታት በፊት
ዲያብሎስ አዳምና ሔዋንን
ፈትኗቸው ነበር። አሁን
ደግሞ ኢየሱስ
ሊፈተን ነው።




ዲያብሎስ
ኢየሱስን እንኳ
ለመፈተን
ሞክሯል።



ዲያብሎስም።
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥
ይህን ድንጋይ። እንጀራ ሁን
ብለህ እዘዝ አለው።ኢየሱስ
እንደተራበ ስላወቀ
ነበር።**ኢየሱስ እሺ ይል
ይሆን?**

እርሱም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ
አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።



ወደ ኢየሩሳሌም ደግሞ ወሰደው። ሰዎችም እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት በመቅደስ ጫፍ ላይ አቆመው። አሁንስ ዲያብሎስ ምን ይለው ይሆን?




ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ
አንተ ያዝልሃል፥ እግርህንም በድንጋይ ከቶ
እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ
ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ
ከሆንህ፥ ከዚህ ወደ ታች
ራስህን ወርውር
አለው።

በፍጹም አለ ኢየሱስ! ኢየሱስም መልሶ፡-
ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ
ተጽፎአል አለው።





ሌላ ሙከራ አደረገ።ዲያብሎስም
ኢየሱስን ረጅም ወደ ሆነ ተራራ
አወጣው። የዓለምን መንግሥታት
ሁሉ በቅጽበት አሳየው።

የዓለምን መንግሥታት
ክብራቸውን ሁሉ
በቅጽበት
አሳየው።ወድቀህ
ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ
እሰጥሃለሁ አለው።



ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው።



ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው፥ እነሆም፥ እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ ለዲያብሎስ ያልተሸነፈውን ልጁን ኢየሱስን እንዲያገለግሉት አደረገ።



# የኢየሱስ መፈተን

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ ወንጌል ምዕ. 4
እና ማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 4

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር
ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው
ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16